*ፕሬስ ሪሊዝ*

*ታህሣሥ 23 ቀን 2000 ዓ.ም*

*ማስታወቂያ ሚኒስቴር*

# <u>የጋራ ውይይቱ መድረክ ቀጣይነት ለልማት ዕድገቱ ስኬት</u>
# <u>የጎላ ድርሻ ይኖረዋል</u>

ሕዝብና መንግሥት ተቀራርበው በመወያየትና በመስራት ሊፈቱዋቸው የማይችሉት ችግሮች ሊኖሩ አይችሉም:: እንዲህ አይነቱ መቀራረብ አገራዊ የጋራ መግባባት በመፍጠር ልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ለማጠናከር የሚኖረው አስተዋጽኦ የጎላ ነው:: ይህንኑ በመገንዘብ መንግሥት ከተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች ጋር በርካታ የውይይት መድረኮችን ከፍቶ ጠቃሚ የሐሳብ ልውውጦችን ማካሔድ ችሏል:: ከመምህራን፣ ከወጣቶች፣ ከሴቶች፣ ከባለሃብቶች፣ ከአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ወዘተ ጋር መንግሥት ያደረጋቸው ውይይቶች የሚታወሱ ናቸው:: በነዚህ የውይይት መድረኮች ሕብረተሰቡን የበለጠ የሚረዳበት ሁኔታ ማጠናከር የሚችልበት ሁኔታ ፈጥሯል::

የአዲስ አበባን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመፍታት መንግሥት ከከተማዋ ነዋሪዎችና የተለያዩ ፎረሞች ተወካዮች ጋር በቅርቡ ያደረገው ውይይት ለህብረተሰቡ ጥያቄዎች ፈጣንና ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት ያለውን ዝግጁነትና ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው::

መንግሥት በዚህና በሌሎችም መሰል መድረኮች ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ውጤታማ ውይይቶችን በማድረግ ህዝቡን ለዘላቂ ልማትና ለውጥ በማነሳሳቱ ከፍተኛ ውጤት የተመዘገበበት መሆኑ ይታወቃል:: እነዚህም መድረኮች በመንግሥትና በህዝቡ መካከል ድልድይ በመሆን የህዝቡን ጥያቄ ለመንግሥት የመንግሥትን አቋም ደግሞ ለህዝብ በማድረስ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል::

መድረኮቹ የህዝብና የመንግሥትን የመደማመጥ ባህልን ከማጎልበት በተጨማሪም ከህዝብ ለሚነሱ ችግሮች የጋራ መፍትሔ ለመስጠት ያስቻሉና በመንግሥት ሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና የልማት ፕሮግራሞች ዙሪያም ለህዝቡ

ግልጽነትን ለመፍጠርና የነዚህ ድምር ውጤት የሆነውን ብሔራዊ መግባባትን በማጠናከር ረገድ የጎላ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ በክልሎች ደረጃም የክልል መስተዳድሮች ከህብረተሰቡ ጋር የሚያደርጓቸው ውይይቶች አበረታች ውጤቶችን እያስገኙ በመሆናቸው ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡

መንግሥት በተለይ በግብይት ሥርዓት የሚከሰቱ ችግሮችን በዘለቄታዊነት ለመፍታትም አምራቹን በቀጥታ ከሸማቹ ጋር ማገናኘት የሚችሉ ጠንካራ የሸማቾች ማህበራት እንዲቋቋሙ ድጋፍ ለማድረግ እንዲሁም የከተማዋን የመልካም አስተዳደርና የልማት ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ዝግጁ መሆኑ ከህዝቡ ጋር ተደጋግፎ ለመስራት ያለውን ቁርጠኛ አቋም የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በከተማዋ መሬት አስተዳደር እየታየ ያለውንም የሙስናና የህገወጥ ግንባታ ተግባር በህብረተሰቡ ጥቆማ መሰረት ለማስተካከል መንግሥት እስካሁን ያደረገው ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በሙሰኞችና በህገወጥ ገንቢዎች ላይም ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡ ለዚህም እውን መሆን ህብረተሰቡ ህገወጥ ግንባታዎች እንዳይካሄዱና መሬትን በጉቦ የሚይዙ ግለሰቦችን በማጋለጥ ረገድ ከፍተኛ ርብርብ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ህብረተሰቡ የተሻለ የመኖሪያና የሥራ ቦታ እንዲያገኝ የሚያስችል ግብ ተይዞ ያረጁ ቤቶችን አፍርሶ የማልማት ሥራም የሚከናወን ሲሆን ከዚህ አንጻር ነዋሪው የተያዘውን ግብ እንዲቀበል በማድረግ በጋራ እቅድ መሥራት ይገባል፡፡ የጋራ ውይይቱ ተጠናክሮ መቀጠልም በዚህ ረገድ ህብረተሰቡን በማሳመንና የጋራ እቅድ በማውጣት ሂደት ግንባር ቀደም ሚና ይጫወታል፡፡

መንግሥት በተለያዩ ጊዜያት ከነዋሪው ጋር ያደረገው ውይይት የተጠናከረ የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ለውጥ ለማድረግ ያስቻለ ሲሆን የውይይቱ ቀጣይነትም አንዳንድ የአሰራር ጉድለቶችንና ማህበራዊ ችግሮችን በመመካከር በዘላቂነት ለመቅረፍ ያስችላል፡፡

የመድረኩ ተሳታፊዎች የከተማዋን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች፣ አስተዳደራዊ ጉድለቶች እንዲሁም የፖለቲካ አመራር ክፍተትና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ ላነሷቸው በርካታ መሰረታዊ ጥያቄዎች በተሰጣቸው ምላሽ የተሰማቸውን እርካታ መግለፃቸውም መንግሥት በቀጣይነትም ችግሮችን

ከነዋሪው ጋር በመነጋገር እልባት ለመስጠት ያለውን ዝግጁነት መገንዘባቸውን ያሳያል፡፡

በመድረኩ ላይ እንደተመለከተው የአዲስ አበባን የመልካም አስተዳደርና ሌሎችም ማህበራዊና የልማት ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታትና ቀጣይነት ያለው የልማት ዕድገት ማስመዝገብ የሚቻለው በከተማዋ ዘላቂና ቋሚ አስተዳደር ሲኖር ነው፡፡ በመሆኑም በቅርቡ በሚካሄደው የማሟያና የአካባቢ ምርጫ ላይ ህዝቡ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ተወካዮቹን ለመምረጥ ከአሁኑ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ በከተማዋ ሥር የሰደዱ ችግሮችም ዘላቂ መፍትሔ የሚያገኙት ህዝቡ በሃቅ ያገለግሉኛል ብሎ የሚመርጣቸው እንደራሴዎቹ የመዲናዋን አስተዳደር ሲጨብጡ ነውና ሁሉም በነቂስ ወጥቶ በምርጫው በመሳተፍ የዴሞራሲያዊ መብቱ ተጠቃሚ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

\#  #  #  #